# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ነሐሴ 9 ቀን 2001 ዓ.ም.

## የሀገርን ለም መሬት ለባዕዳን እያሸጠ ያለውን የወያኔ አገዛዝ በጋራ እናውግዝ

ፀረ ሕዝቡ የመለስ አገዛዝ የሀገራችንን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሲሰጥ በተሰጠው መሬት ላይ ማንም እይኖርበትም ብሎ በአሳፋሪ መንገድ ማጠየቂያ ሊፈልግ እንደቃጣው ሁሉ ዛሬ ደግሞ ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ለ8000 የውጭ ኩባንያዎች ሊያስረክብ ሲነሳ ኢትዮጵያ ያልታረሰ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር መሬት አላት ብሎ ሊያደናግር ሞክሯል፡፡

ባለፈው ሳምንት ኢሕአፓ የወያኔን ድርጊት አውግዞ መግለጫ ካወጣ በኋላ ወያኔ ይህን ለማስተባበል በግብርና ሚኒስቴር ባለሥልጣኖቹ አማካይነት በሰጠው መግለጫ ለባዕዳን መሬት መስጠቱ በኢትዮጵያ ረሀብና ችግርን ያስወግዳል፤ ገቢ ያስገኛል፤...ወዘተ በሚል ደግ ሰራሁ ብሎ ሊመፃደቅ ሞክሯል፡፡ ይህን የሀገርን ለም መሬት አሳልፎ ለባዕዳን የመስጠቱን እርምጃ የተባባሩት መንግሥታት ተቋሞችና ሌሎችም ቢሆኑ ስህተት ነው ሲሉ ትችት መስጠታቸው የሚታወቅ ነው፡፡ የወያኔ ባልሥልጣኖች ሸፋፍነው የሚያልፉቱ ሐቅ የባዕድ አራሾቹ ምርቱን የሚወስዱት ወደ ሀገራቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለኢትዮጵያ ምርትን ከመጨመር አንፃር የሚጠቅመው የለውም፡፡ መሬት በመሸጡ ገቢው ለወያኔ ባልሥልጣኖች እንጂ ለሕዝብ አይደለም፡፡ የሳውዲ ዓረብያ ባለ እርሻዎች በኢትዮጵያ አምርተው ወደ ሀገራቸው መውስዳቸው ታይቷል፡፡ ሕንድ፥ ቻይና፥ የአረብኤሚሬት፥ ደቡብ ኮሪያ፥ ሳውዲ አረቢያ ሁሉም የኢትዮጵያን ለም መሬት በእጃቸው አስገብተው ለመጠቀም እየተሯሯጡ ናቸው፡፡ እስካሁን 2000 የባፅድ ኩባንያዎች የኢትዮጵያን መሬት በእጃቸው አስገብተዋል፡፡ ምርታቸው ለራሳቸው ነው፡፡ ታዲያ ይህ ለኢትዮጵያ ምን ይጠቅማል?

ኢሕአፓ ይህን የወያኔ የሀገርን መሬት የመሸጥና ለባዕዳን አሳልፎ የመስጠት ፀረ ሕዝብ ድርጊት አጥብቆ የሚያወግዘው ድርጊቱ ለሀገርና ለሕዝብ ምንም የሚጠቅም ባለመሆኑ ነው፡፡ ባዕዳን አምርተው ምርቱን ወደ ሀገራቸው እስከወሰዱ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያገኘው ጥቅም የለም፡፡ በመሬት ሽያጩ ተጠቃሚ ወያኔ ራሱ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የሀገርን ለም መሬት ለባዕድ አሳልፎ መስጠቱ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ወያኔያው እርምጃ በመሆኑ ኢሕአፓ አጥብቆ ይኮንነዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም መሬቱንና ጥቅሙን ለማስከበር አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስድ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርጋል፡፡

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com